የሰ/መ/ቁ. 37027

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ግርማ ማርቆስ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አሰለፈች ደስታ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት የሥራ ክርክር ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ለፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ የወሰደባቸው የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲሻር፣ ተጠሪ ወደ ቀድሞ የስራ መደብ እንዲመልሳቸው እና የተቋረጠውን የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደባቸው ጥፋተኛነታቸው ተረጋግጦ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች የወሰደውን እርምጃ አሻሽሎ ተጠሪ በ4 ቀን ደመወዝ እንዲቀጡና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ወደ ቀድሞ ስራቸው እንዲመለሱ፣ በደመወዝ ላይ የተደረገው ጭማሪም ተስተካክሎ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የአመልካችን ይግባኝ ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ በህብረት ስምምነቱ የጥፋት አይነቶችና የቅጣት ደረጃዎች ተዘርዝረዋል፡፡ አንድ ሰራተኛ ጥፋት ሲፈጽም እርምጃ የሚወሰድበት ስለጥፋት አይነቶች እና ስለ ቅጣት በሚያስረዳው ሰንጠረዥ መሰረት ሲሆን የጥፋቱን ክብደት ከሚያሳዩት ደረጃዎች ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነውን ቅጣት መቅጣት ይቻላል፡፡ የጥፋት አይነቶች እና የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡት የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት ለመመዘን እንዲያመች እንጂ የጥፋት ቅደም ተከተልን ለመወሰን አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ ስህተቱ የተፈጠረው በእርሣቸው ስህተት ባለመሆኑና ከድርጅቱ የውስጥ አሰራርና አመራር ጉድለት በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በህ/ስምምነት ውስጥ ከተዘረዘሩት የቅጣት አይነቶች ቅደም ተከተል ሣይጠበቅ በአንድ ጥፋት በ4ኛ ደረጃ የተቀመጠውን ቅጣት እንዲቀጡ መወሰኑ ሕጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የቅጣት ደረጃው ቅደም ተከተልን የሚያሣይ ሣይሆን በተፈፀመው ጥፋት ክብደት ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን የተቀመጡ ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደተቻለው የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥፋተኛነት ተቀብሎ ወደ ቅጣት ውሣኔው ትክክለኛነት አምርቷል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ሊቀጡ የሚገባው የህ/ስምምነቱ ከዘረዘረው ቅጣቶች በቅደም ተከተል ነው ወይስ ህ/ስምምነቱ እንደጥፋቱ ክብደት ቅደም ተከተል ሣይጠበቅ ቅጣቱ ይጣል የሚለው ነ1ው፣ አከራካሪ የሆነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤትም በሰጡት መልስ ምንም የፈፀሙት ጥፋት የሌለ ከመሆኑ ውጪ ቅጣቱ በምን ሁኔታ መፈፀም እንዳለበት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የተጠሪን ጥፋተኛነት አረጋግጠው በሰጡት ውሣኔ ላይም የቀረበ አቤቱታ ባለመኖሩ ተጠሪ ጥፋተኛ ናቸው አይደለም ወደሚለው ነጥብ መግባት አስፈላጊ አይሆንም፡፡ አንድ ሰራተኛ

ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣቱ እንዴት ነው ሊወሰን የሚገባው የሚለውን ስንመለከት የአመልካች መ/ቤት ህብረት ስምምነት እንደሚያሣየው ለተለያዩ የጥፋት አይነቶች የተለያዩ ቅጣቶች ተመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የተመደቡበትን ስራ በቸልተኛነት አለመስራት ጥፋት ለምሣሌ በ5 የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች ሊያስቀጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም በመ/ቤቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 22(12)(ሀ) ሥር በአንድ ሰራተኛ ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ሲወሰድ የሚወሰነው ቅጣት ስለጥፋትና ስለቅጣት አይነት በሚያስረዳው ሰንጠረዥ መሰረት ሆኖ የጥፋቱን ክብደት ከሚያሣዩት ደረጃዎች ለጥፋቱ ተመጣጣኝ በሆነ የቅጣት ደረጃ ሊቀጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ስለጥፋትና ስለቅጣት አይነት በሚያሣየው ሰንጠረዥ ግርጌም የቅጣት ደረጃው የሚያመለክተው እንደጥፋቱ ክብደትና ቀላልነት የጥፋቱን ደረጃና ለደረጃውም የሚወሰነውን ቅጣት እንጂ የጥፋት ቅደም ተከተልን እንዳልሆነ በማሳሰቢያነት ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም ከህ/ስምምነቱ አንድ ሰራተኛ ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ ቅጣቱ የሚጣልበት በሰንጠረዡ ላይ በሰፈረው ደረጃ ቅደም ተከተል ሣይሆን የጥፋቱ ክብደት ታይቶ ተመጣጣኝ ነው ተብሎ በሚገመተው የቅጣት ደረጃ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

በተያዘው ጉዳይም አመልካች ተጠሪ በቸልተኛነት ሥራ ባለመስራት በመ/ቤቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረሣቸው የጥፋታቸው ክብደት በደረጃ አራት ላይ የተመለከተውን የቅጣት አይነት ያስቀጣቸዋል በማለት በዚሁ መሰረት እርምጃ ወስዷል፡፡ የጥፋቱን ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት የመወሰን ተግባር ደግሞ ለአሰሪው ሊተው የሚገባ አስተዳደራዊ ስራ መሆኑን እናምናለን፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ ጥፋተኛ ለሆነበት ድርጊት የተመለከተውን ቅጣት መወሰኑ ህገ ወጥ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የህብረት ስምምነቱን በአግባቡ ሣያጤኑ ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው በቅደም ተከተል ነው በማለት የሰጡት ውሣኔም ከላይ በሰፈሩት ምክንያቶች ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21035 በሐምሌ 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58454 በየካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ የወሰደው እርምጃ የህ/ስምምነቱን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም ፡፡
3. ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ